# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን

# የአካባቢ ድምፅ ብክለት ክትትልና ቁጥጥር አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር ፩. ፳፻፲፩ ዓ.ም

**አዲስ አበባ**

ጥር፣ 2011 ዓ.ም

## ክፍል አን

### መግቢያ

በዓለም ላይ የከተሞች እድገት በመጠንም ሆነ በቁጥር እጅግ ፈጣን እየሆነ መጥቷል፡፡ የኢኮኖሚና የማህበራዊ አውታሮች እድገትም በአብዛኛው በከተሞች አካባቢ ጎልቶና ተከማችቶ ይታያል፡፡ የከተሞች የህዝብ ብዛት እድገትም ከጊዜ ወደ ጊዜ በፍጥነት እየጨመረ ይገኛል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የመኖሪያ ቤት እጥረትና የአካባቢ ብክለት በከተሞች አካባቢ እጅግ የከፋ ችግር ሆኖ ይገኛል፡፡ በአገራችን ከሚከናወኑ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ተቋሞች መካከል አብዛኞቹ በከተሞች አካባቢ የሚገኙ ናቸው፡፡ በተለይም አዲስ አበባ እንድታድግ እድል ከፈጠሩላት በርካታ ምክንያቶች በመነሳት ሰፊ የማህበራዊና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚደረግባት ከተማ በመሆኗ በአገሪቱ ውስጥ ከሚከናወኑት የልማት ስራዎች አብዛኞቹ በከተማዋ ይገኛሉ፡፡ እነዚህን በከተማዋ በመስፋፋት ላይ የሚገኙ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ተከትሎ በርካታ ህዝብ ከገጠር ወደ ከተማ እየፈለሰ የሚኖርባት እና የመኖሪያ ቤት እጥረት ያለባት ከተማ በመሆኗ ነዋሪዎች ደረጃዎችን ባልጠበቁና ባልተሟሉ ቤቶች ተፋፍገው ይኖሩባታል፡፡ የዚህ ዓይነቱ አኗኗር ከዓለም ሙቀት መጨመር ጋር ተደምሮ ከሚያስከትለው ጫና በተጨማሪ በከተማችን ከሚከናወኑት የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች የሚመነጩ ለአካባቢ ደህንነት የማይበጁ፣ በጤናማና ባልተበከለ አካባቢ የመኖር ህገ መንግስታዊ መብትን የሚያቃውሱ በርካታ የአካባቢ ብክለት ችግሮች በመከሰት ላይ ይገኛሉ፡፡

በከተማችን ከሚስተዋሉ የብክለት አይነቶች መካከል በዋነኛነት የድምፅ ብክለት ተጠቃሽ ነው፡፡ የድምፅ ብክለት ማለት ማንኛውም ሰው በስራ ሰዓት፣ በእረፍት ፣ በእንቅልፍ ፣ በመዝናኛና በመሳሰሉት ማህበራዊ እንቅስቃሴ ወቅት ጣልቃ በመግባት የስነልቦናና የአካል ጉዳት በሰዎች ላይ ሊያደርስ የሚችል ያልተፈለገና ከደረጃ በላይ የሆነ ድምጽ ማለት ነው፡፡ የድምፅ ብክለት ከሀይማኖት ተቋማት፣ ከማምረቻ ተቋማት፣ ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና ከሌሎችም ይመነጫል፡፡ በመሆኑም የድምፅ ብክለትን ችግር ከወዲሁ ለመግታት በፌዴራል መንግስት ከወጡት የአካባቢ ህጎች በተጨማሪ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ከከተማዋ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት በአካባቢ ደህንነት ላይ ያተኮሩ በርካታ ደንቦችን አውጥቷል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 25/2000 ነው፡፡ ይህን ደንብ ለመተግበር ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህን የአካባቢ ድምፅ

ብክለት ቁጥጥር አፈጻጸም መመሪያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃና የአረንጓዴ ልማት ኮሚሽን አውጥቷል፡፡

1. **ጠቅላላ**

ይህ መመሪያ የአካባቢ ድምፅ ብክለት ቁጥጥር አፈጻጸም መመሪያ ተብሎ ለጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

2.1.አስተዳደርኝ ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡

2.2. ከተማ ማለት አዲስ አበባ ነው፡፡

2.3.ኮምሽን ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን መ/ቤት ነው፡፡

2.4.አካባቢ.ማለት በመሬት፣ በከካባቢ አየር፣ በአየር ሁኔታና በአየር ንብረት፣ በውሃ በህያዋን፣ በድምጽ፣ በሽታ፣ በጣዕም፣ በማህበራዊ ጉዳዮች እና በስነውበት ሳይወሰን በተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች ወይም በሰው አማካኝነት ተሻሽለው ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በጠቅላላ ያሉበት ቦታ፣ እንዲሁም መጠናቸው ወይም ሁኔታቸው፣ የሰው ወይም የሌሎች ህያዋን በጎ ሁኔታን የሚነኩ መስተጋብሮቻቸው ድምር ነው፡፡

2.5.የአካባቢ ድምጽ መበከል ማለት በውል ታስቦም ይሁን ሳይታሰብ የድምፅ ብክለት ወደ ማንኛውም የአካባቢ ክፍል መልቀቅ ነው፡፡

2.6.የአካባቢ ተቆጣጣሪ ማለት በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር በደንብ ቁጥር 25/2000 አንቀጽ 12 መሰረት ባለስልጣኑ በአካባቢ ብክለት ተቆጣጣሪነት የተመደበ ሰራተኛ ነው፡፡

2.7. ሰው ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

2.8.የአካባቢ ድምጽ ደረጃ ማለት በአካባቢ መኖር ያለበት የድምጽ መጠን፣ ያጠ ቃልላል፡፡

2.9.የአካባቢ ክፍል ማለት የአካባቢ አካል የሆነ እንደ መሬት፣ ውሃ፣ አየር እና በውስጣቸው የሚይዟቸውን ህያውና ግዑዝ አካላትን ያጠቃልላል፡፡

## 3. ዓላማ

- ከድምፅ ብክለት ጋር በተያያዘ የወጣውን አዋጅ መሰረት በማድረግ፣ በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ዘንድ የሚነሱ ቅሬታዎችንና ጥቆማዎች ወይም የድምፅ ብክለት ያደርሳሉ ተብለው የሚገመቱ ተቋማት፣ ድርጅቶችና ሌሎችንም አካላት ላይ በወጣው የድምፅ ደረጃ መነሻነት ህግን ማስከበር።

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ አካባቢ ሊበክሉ የሚችሉ ድምጽ በማመንጨት ወይም በማውጣት በአካባቢ ደህንነት ላይ የድምጽ ብክለት እና ሌሎች አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ሊያስከትሉ ይችላሉ ተብለው በሚገመቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ በሚገኙ ማምረቻ ድርጅቶች፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 5. የድምጽ ብክለት አያያዝና አወጋገድ ስርዓት

### 5.1. ድምጽ ብክለት

5.1.1. ማንኛውም ሰውና ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው ተቋም ወይም ድርጅት በስራ ሰዓት፣ በእረፍት፣ በእንቅልፍ፣ በመዝናኛና በመሳሰሉት ማህበራዊ እንቅስቃሴ ወቅት ጣልቃ በመግባት የስነልቡናና የአካል ጉዳት በሰዎች ላይ ሊያደርስ የሚችል፣ ያልተፈለገና ከተቀመጠው ደረጃ በላይ የሆነ ድምጽ መልቀቅ አይችልም፡፡

5.1.2. ማንኛውም ሰው በመሰብሰቢያ አዳራሾች በመማሪያ ክፍሎችና በመኖሪያ ቤቶች ድምፅ ለመቀነስ የሚያስችሉ ዘዴዎች መጠቀም ይኖርበታል፡፡

5.1.3. በሥራ ባህርይው ምክንያት ከፍተኛ ድምጽ እንዲመነጭ የሚያደርግ ማንኛውም ሰው በድምጽ ምንጭና አድማጩ መካከል ያለውን ርቀት መጨመር፣ ድምጽ የሚያልፍበትን መንገድ መዝጋት፣ ድምጽን ከምንጩ መቀነስ፣ ድምጽን መቀነስ የሚያስችል ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምና ዝቅተኛ ድምጽ የሚያመነጩ መጓጓዣዎችንና ማሽኖችን ወደ አገር ውስጥ አስገብቶ መጠቀም ይኖርበታል፡፡ ከደረጃ በላይ የሆነ ድምጽ የሚያመነጩ

መጓጓዣዎች፣ ማሽኖችና እንዱስትሪዎች ህዝብ በሚንቀሳቀስባቸዉ ስፍራዎች መጠቀም አይኖርበትም፡፡

## 5.2. የአካባቢ የድምፅ ብክለት ደረጃ

| የድምፅ ልቀት መጠን በዴሲቢል ( limits in dB(A) leq ) | | | |
|---|---|---|---|
| የአካባቢ ኮድ<br>(Area code) | የአካባቢ ክፍል<br>(category of area) | በቀን(ከጧት 12ሰዓት እስከ ማታ 03 ሰዓት)<br>(Day time) | በማታ(ከምሽቱ 03 ሰዓት በኋ እስከ ጧት12 ሰዓት)<br>(Night time) |
| ሀ | የኢንዱስትሪ አካባቢ(Industrial area) | 75 | 70 |
| ለ | የንግድ ተቋማት (commercial area) | 65 | 55 |
| ሐ | የመኖሪያ አካባቢ(residential area) | 55 | 45 |

ማሳሰቢያ፡- የድምፅ ብክለት የደረሰበት አካባቢ ቅይጥ ከሆነ፡-

- የመኖሪያ አካባቢና የንግድ አካባቢ በጣምራ ከሆነ በመኖሪያ ቤት የልኬት ደረጃ ይለካል፡፡
- የመኖሪያ አካባቢና የኢንዱስትሪ አካባቢ በጣምራ ከሆነም በመኖሪያ ቤት የልኬት ደረጃ ይለካል፡፡
- የንግድ አካባቢና የኢንዱስትሪ አካባቢ በጣምራ ከሆነ በንግድ አካባቢ የልኬት ደረጃ ይለካል፡፡
- የመኖሪያ አካባቢ፣ የንግድ አካባቢና የኢንዱስትሪ አካባቢ በጣምራ ከሆነ በመኖሪያ ቤት የልኬት ደረጃ ይለካል፡፡

# ክፍል ሦስት

# 6. የድምጽ ብክለት ቁጥጥር መነሻዎች

## 6.1. ጥቆማ ወይም አቤቱታ

### 6.1.1. ጥቆማ

ሀ. ማንኛውም የተፈጥሮ ሰውና ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው ተቋም ወይም ድርጅት የድምጽ ብክለት መድረሱን ካወቀ ወይም ይደርሳል ብሎ ከገመተ ለኮሚሽን መ/ቤቱ ወይም በየደረጃው ለሚገኙ የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን ጽ/ቤቶች በሚያመቸው መንገድ በስልክ ወይም በአካል ቀርቦ በቃል ወይም በሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች ጥቆማውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

ለ. ጠቋሚው የድምጽ ብክለት አለ ብሎ የገመተውን አካባቢ፣ ክ/ከተማ፣ ቀበሌውንና የአካባቢውን ልዩ ስም ከተቻለም የድምፅ ብክለት የለቀቀውን ወይም ሊለቅ ይችላል ብሎ ያሰበውን በካይ አካል ስም መግለጽ ይኖርበታል፡፡

ሐ. ጠቋሚው በሰጠው ጥቆማ የተወሰደውን የማስተካከያ እርምጃ የመጠየቅና የማወቅ መብት አለው፡፡

መ. ጠቋሚው ለሰጠው ጥቆማ ማስረጃ እንዲያቀርብ አይገደደም፡፡

ሠ. ጠቋሚው ካልፈቀደ በስተቀር ስሙንና አድራሻውን እንዲገልጽ አይገደደም ስሙ እንዳይገለጽ ከአሳወቀም የጠቋሚው ስም በሚስጥር ይያዛል፡፡

### 6.1.2. አቤቱታ

ሀ. ማንኛውም ሰው በሚኖርበት፣ በሚሰራበት፣ በሚዝናናበትና ሌሎች ማህበራዊ ተግባራትን በሚፈጽምበት ወይም በሚንቀሳቀስበት አካባቢ የደረሰ የድምጽ ብክለት እንዲወገድለት በጋራም ሆነ በተናጠል ለኮሚሽን መ/ቤት ወይም በየደረጃው ለሚገኝ የኮሚሽኑ ፅ/ቤቶች አቤቱታ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

ለ. የድምፅ ብክለት መድረስ አለመድረሱ ባይረጋገጥም አካባቢን ሊበክል ይችላል ተብሎ የሚገመትን የድምጽ ልቀት መኖሩን ከአወቀ ወይም አካባቢን ሊበክል ይችላል ተብሎ የሚገመት ድምጽ ሊለቀቅ ይችላል ብሎ ከሰጋ አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

ሐ. በጽሁፍ የሚቀርብ አቤቱታ ድምጽ የተለቀቀበትን አካባቢ፣ ክ/ከተማ፣ ቀበሌውን እና የቦታውን ልዩ ስም፣ ድምጽ መለቀቅ የጀመረበት ጊዜ፣ የሚለቀቀው ድምጽ የሚለቀቅበትን ወቅት፣ የሚቻል ከሆነም ብክለቱ ያደረሰውን ጉዳት በዝርዝር ማካተት ይችላል፡፡

መ. አቤቱታ የሚቀርበበትን ቅጽ መ/ቤት ያዘጋጃል፤ ሆኖም አቤቱታ አቅራቢው በመሰለው መንገድ በጽሁፍ አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

ሠ. አቤቱታ አቅራቢው በአቤቱታው ላይ መፈረም ይኖርበታል፡፡

ረ. አቤቱታ አቅራቢው የአቀረበውን አቤቱታ አፈጻጸም የመከታተልና ውጤቱንም የማወቅ መብት አለው፡፡

## 6.2. በኮምሽን መ/ቤት የድምጽ ብክለት ቁጥጥርና ክትትል ስርዓት መነሻ

6.2.1. በኮሚሽኑ የተመደቡ የአካባቢ የድምጽ ብክለት ኢንስፔክተሮች ማንኛውንም ማምረቻ፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋምና ሌሎችንም በማንኛውም ጊዜ ከድምጽ ብክለት ጋር በተያያዘ ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋሉ፡፡

6.2.2. በንዑስ ቁጥር 6.2.1. የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በክፍለ ከተማና ወረዳ ያሉ የኮሚሽኑ ፅ/ቤት ኢንስፔክተሮች የድምፅ ልቀት ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ ስልጣንና ኃላፊነት የተሰጣቸው ሲሆን፣ የሚወስዱትም አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ ለኮሚሽኑ የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

6.2.3. በተለይም የድምጽ ብክለት ሊያደርሱ ይችላሉ ተብለው በሚገመቱ የማምረቻ፣ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ሌሎችም ላይ መደበኛ የቁጥጥርና የክትትል ፕሮግራም በማውጣት ቁጥር ይደረጋል፡፡

# ክፍል አራት

## 7. የቁጥጥርና ልኬት ስርዓት

### 7.1. ተቆጣጣሪው የድምጽ ብክለት ቁጥጥር በሚያደርግበት ጊዜ ሊያሟላቸው የሚገቡ ሁኔታዎች

7.1.1. የድምጽ ብክለት ቁጥጥር ለማድረግ ተቆጣጣሪው ሲንቀሳቀስ የአካባቢ ብክለት ተቆጣጣሪ ስለመሆኑ ከኮሚሽን መ/ቤት ወይም በየደረጃው ከሚገኝ

የኮሚሽኑ ፅ/ቤቶች የተሰጠ መታወቂያ መያዝና ቁጥጥር ለሚደረግበት አካል የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡

7.1.2. ተቆጣጣሪው ለስራው አፈጻጸም ደህንነትና መሳካት አስጊ ሆኖ ካገኘው የፍትህ አካላትና አስፈላጊ ሰራተኞችን ይዞ የቁጥጥርና ልኬት ስራውን ሊያከናውን ይቻላል፡፡

## 7.2. ቁጥጥርና ልኬት ስለማድረግ

7.2.1. የድምጽ ብክለት ተቆጣጣሪው መደበኛ የቁጥጥር ፕሮግራም በማውጣት ወይም ድንገተኛ የቁጥጥር ስልት በመቀየስ የስራ ባህርይው በአካባቢ ላይ ድምጽ ብክለትን እንዲሁም በሰው ልጅ አኗኗር፣ ጤንነት እና ደህንነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያደርሱ ይችላሉ ተብለው በሚገመቱ፣ ድርጅቶች ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጣቸው ተቋማት ላይ በማንኛውም ቀንና ሰዓት ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የድምጽ ልኬት ይወስዳል፡፡

7.2.2. ተቆጣጣሪው ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የድምጽ ልኬት በሚያካሂድበት ወቅት ተቋሙ ወይም ድርጅቱ መደበኛ ስራውን በተለመደው አኳኋን ማካሄድ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ግን ቁጥጥርና ልኬት በሚካሄድበት ወቅት ተቋሙ ወይም ድርጅቱ ስራ አቁሞ ወይም ማሽን ቀዝቅዞ ከሆነ እና የማሽኑ መነሳት ለቁጥጥሩ ስራ አስፈላጊ መሆኑን ተቆጣጣሪው ካመነበት ማሽኑ እንዲነሳ መደረግ አለበት፡፡

7.2.3. የድምጽ ብክለት ተቆጣጣሪው ቁጥጥርና ልኬት ካደረገ በኋላ ተቋሙ ወይም ድርጅቱ ያለበትን ሁኔታ ገምግሞ የአካባቢ ብክለት እያደረሰ መሆን አለመሆኑን በማረጋገጥ ከደረጃ በላይ የድምፅ ልቀት ብክለት ባደረሱ፣ ድርጅቶች ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጣቸው ተቋማት ላይ በማንኛውም ቀንና ሰዓት ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ አስተዳደራዊ ውሳኔ የድምፅ ብክለት ላደረሰው አካል ይገለፅለታል፡፡ ቁጥጥር የተደረገው በአቤቱታ መነሻነት ከሆነ የዚሁ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

# ክፍል አምስት

## 8. የአከባቢ የድምጽ ብክለት ልኬት አወሳሰድ ሁኔታ

## 8.1. የአካባቢ የድምጽ ብክለት ልኬት

8.1.1.ጉዳቱ ወይም ብክለቱ የደረሰበት ቦታ ወይም አካባቢ ሆኖ መለካት አለበት፡፡

8.1.2. በድምጽ ብክለት ተጠቂ ነው ተብሎ የሚታመን ከሆነ የድምጽ ብክለት ለመከላከል የትም ቦታ ሆኖ መለካት ይቻላል፡፡

8.1.3. የድምጽ ብክለት የሚያደርሱ ማንኛውም አካላት ወይም ተቋማት በብዛት አንድ አካባቢ የሚገኙና በተመሳሳይ ሰዓት የድምጽ ብክለት የሚያደርሱ ከሆነ፣ በተናጠል የድምፅ ልኬት ለመውሰድ ተቆጣጣሪው ባለሙያ የድምጽ ብክለቱን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በመታገዝ በተናጠልም ሆነ ሁሉንም በአንድ ላይ በመለካት ብክለቱ በደረሰበት ቤት እና ቦታ ላይ ወይም የድምፅ ብክለት ይደርስበታል ብሎ በገመተው ቦታ ሆኖ በመለካት እርምጃ መውሰድ ይቻላል፡፡

## 8.2. የአካባቢ ድምጽ ብክለት የእርምጃ አወሳሰድ ሁኔታ

8.2.1. ልኬቱ ከተወሰደ በኋላ ለአካባቢው ከተፈቀደለት እስታንዳርድ ወይም ደረጃ በላይ ሆኖ ከተገኘ ለአምራች ድርጅት፣ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና ለሌሎች የድምጽ ብክለት አመንጪ ለሆኑ አካላት አፋጣኝ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፡፡

8.2.2. የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው አካል ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው ጊዜ ጀምሮ ለአገልግሎት ሰጭ ተቋማት 2(ሁለት) ቀን እና ለፋብሪካዎች 15 (አስራ አምስት) ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የድምጽ ብክለቱን በማስቆም፣ ችግሩን ፈትቶ ማስጠንቀቂያ ለጻፈው ኮሚሽን መ/ቤት ያስተካከለበትን መረጃ ሪፖርት በጽሁፍ እና በአካል ማቅረብ አለበት፡፡ ነገር ግን የአምራች ድርጅቶች አሳማኝ ምክንያት ካቀረቡ ጉዳዩ ለኮሚሽን መስሪያ ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ቀርቦ በግዴታ ውል ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡

8.2.3. በ7.2.2. የተገለፀው ሳይፈፅም ቢቀር የድምፅ ብክለት አድራሹ አካል ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

8.2.4. የመጀመሪያ የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በድጋሚ ለሁለተኛ ጊዜ ልኬት ተወስዶ በክሎ ከተገኘ፣ የአምራች ድርጅቶች በ24 ሰዓት፣ አገልግሎት ሰጭ ተቋማትና ሌሎች ደግሞ በ12 ሰዓት ውስጥ የሚበላሸን ንብረት እንዲያወጣ ተደርጎ ድርጅቱ ወዲያውኑ ይታሸጋል፡፡

8.2.5. ለመጀመሪያ ጊዜ የታሸገ ተቋም ወይም ድርጅት ከ5 ቀን በላነሰና ከ3 ወር ባልበለጠ ሊከፈት ይቻላል፡፡

8.2.6. አንድ የተፈጥሮ ሰው የዚህን አዋጅ ወይም በስሩ የሚወጡትን ደንቦች በመተላለፍ የድምፅ ብክለት ወደ አካባቢ በመልቀቅ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ከ1000(አንድ ሺ) ብር በማያንስና ከ5000(አምስት ሺ) ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማያንስና ከአስር አመት በማይበልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡ ጥፋቱን የፈጸመው በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ከ5000 (አምስት ሺ) ብር በማያንስና ከ25000(ሀያ አምስት ሺ) ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡ የስራ ሀላፊውም ከ5(አምስት) ዓመት በማያንስና ከ10 (አስር) ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም ከ5000(አምስት ሺ) ብር በማያንስና ከ10000(አስር ሺ) ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

አስተዳደራዊ እርምጃ የወሰደው ኮሚሽን መ/ቤት የአካባቢ ድምጽ ብክለት ካደረሰው ተቋም ጋር የግዴታ ውል መፈራረም አለበት፡፡ መልሶ ከበከለ ግን አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል፡፡

8.2.7. በንዑስ ቁጥር 7.2.6. እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው ተቋም ወይም ድርጅት የድምፅ ብክለቱን ለመጀመሪያ ጊዜ ካደረሰ ብር 5000(አምስት ሺህ ብር) እና የውዴታ ግዴታ ስምምነት ፈፅሞ እሽጋው ይነሳለታል፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ከፈፀመ፣ 25000(ሃያ አምስት ሺህ ብር) ከተቀጣ በኋላ፣ የውዴታ ግዴታ ስምምነት ፈፅሞ እሽጋው ይነሳለታል፡፡ ለሶስተኛ ጊዜ ከሆነ ድርጅቱም የስራ ኃላፊውም በጣምራ በህግ(በፍትሐ ብሔር እና በወንጀል) እንዲጠየቅ ይደረጋል፡፡

8.2.8. በንዑስ ቁጥር 7.2.6. እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ የተፈጥሮ ሰው የድምፅ ብክለቱን ለመጀመሪያ ጊዜ ካደረሰ ብር 1000(አንድ ሺህ ብር) እና የውዴታ ግዴታ ስምምነት ፈፅሞ እሽጋው ይነሳለታል፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ከፈፀመ፣

5000(አምስት ሺ.ህ ብር) ከተቀጣ በኋላ፣ የውዴታ ግዴታ ስምምነት ፈፅሞ እሽጋው ይነሳለታል፡፡ ለሶስተኛ ጊዜ ከሆነ በፍትሐ ብሔር እና በወንጀል እንዲጠየቅ ይደረጋል፡፡

8.2.9. ማንኛውም ሰው፣ ህጋዊ ስውነት የተሰጠው ድርጅት ወይም ተቋም በድምፅ ብክለት ምክንያት የተወሰደውን አስተዳደራዊ የማሸግ እርምጃ ውሳኔ በመተላለፍ የታሸገውን ገንጥሎ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ተደብቆ ሲሰራ የተገኘ፣ በወንጀል እንዲጠየቅ ያደርጋል፡፡

8.2.10. በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል፣ ተቋም ወይም ድርጅት በአካበቢ ላይ የድምጽ ብክለት አድርሶ ለሶስተኛ ጊዜ የድምፅ ብክለት አድርሶ ከተገኘ፣ የንግድ ፈቃዱ በፈቃድ ሰጪው አካል እንዲሰረዝ ማስደረግ አለበት፡፡

## 9. ለድምጽ ብክለቱ ምክንያት የሆነውን ነገር ስለመያዝ

9.1. ተቆጣጣሪው አካል የድምጽ ብክለት ቁጥጥር በሚያደርግበት ወቅት በአካባቢው ከሚፈቀደው ደረጃ በላይ አካባቢን ሊበክል የሚችል እቃ ሊይዝ ወይም እንድያዝ ሊያደረግ ይችላል፡፡

9.2. በአካባቢው ላይ የደረሰው ወይም እየደረሰ ያለው የድምጽ ብክለት ድምጹን ለማጉላት ጥቅም ላይ የዋለውን ማንኛውም ዓይነት ድምጽ ማጉሊያ፣ ቴፐሪከርደር ወይም ሲዲ ማጫዎቻዎች ወይም ሌሎች ከፍተኛ ድምጽ የሚያመነጩ ወይም የሚያጎሉ መሳሪያዎችን ተቆጣጣሪው ለመያዝ ወይም እንዲያዙ ማድረግ ይችላል፡፡

## 10. የንብረቶች መያዝ የሚኖረው ውጤት

10.1. ንብረቱ የተያዘበት ሰው ንብረቱ በተያዘ በ15 ቀን ውስጥ ቀርቦ ንብረቱ እንዲመለስለት ካመለከተ፣ የተያዘውን ንብረት ዋጋ 20% በመክፈል ከመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ጋር ንብረቱ ይመለስለታል፡፡

10.2. በንዑስ አንቀጽ 9.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ገንዘብ ከፍሎ ንብረቱን መውሰድ የሚችል ሲሆን፣ ነገር ግን በአካባቢው ላይ ባደረሰው ብክለት ምክንያት በህግ የሚኖርበትን ተጠያቂነት አያስቀረውም፡፡

10.3. የንብረት ይመለስልኝ ጥያቄ ማቅረቢያ ጊዜ ከአለፈ በኋላ የቀረበ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፤ ሆኖም ግን የንብረት ይመለስልኝ ጥያቄው በወቅቱ ያልቀረበው ከአቅም በላይ በሆነ አሳማኝ ምክንያት ከሆነና ንብረቱ ያልተወገደ ከሆነ ጥያቄው ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ቀርቦ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

10.4. በተያዘው ጊዜ ውስጥ የንብረት ይመለስልኝ ጥያቄ ያልቀረበባቸውና ያልተመለሱ ንብረቶች ውስጥ ጠቀሜታ ያላቸው ተለይተው በጨረታ ተሸጠው ገንዘቡ ለመንግስት ገቢ ይሆናል፡፡ ጠቀሜታ የሌላቸው ደግሞ በአግባቡ እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡

# ክፍል ስድስት

## 11. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 11.1. ስለማበረታቻ

11.1.1. በስራ ባህርያቸው ምክንያት አካባቢ በድምፅ እንዳይበከል ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያደርጉና ውጤታማ የሆኑ የማምረቻ ድርጅቶችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ኮሚሽን መ/ቤቱ በየዓመቱ እየመረጠ የምስክር ወረቀትና ሌሎች የማበረታቻ ሽልማቶችን ይሰጣል፤ ተግባራቸውም ከአካባቢ ጋር የተጣጣመ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ይሰጣቸዋል፡፡

11.1.2. በአካባቢ ላይ በሚደርስ የድምፅ ብክለት ተቆርቁረው ለኮሚሽኑ መረጃ በመስጠት ተቆርቋሪነታቸውን በተጨባጭ የሚያሳዩ ወገኖችን በመለየት ኮሚሽን መ/ቤቱ የምስጋና ደብዳቤና ሌሎች ማበረታቻዎችን ይሰጣል፡፡

### 11.2. የመተባበር ግዴታ

11.2.1. በአካባቢ ድምጽ ብክለት ላይ ለሚደረገው የቁጥጥርና ክትትል እርምጃ የፖሊስ አባላትና የደንብ ማስከበር ሰራተኞች በማንኛውም ጊዜ ለሚቀርብላቸው የትብብር ጥያቄ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

11.2.2. ማንኛውም ሰው የኮሚሽን መ/ቤት ወይም ተቆጣጣሪው የአካባቢ ድምጽ ብክለት ቁጥጥር በሚያደርግበት ጊዜና ሁኔታ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

12. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከጥር 23፣ 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

የክብርት ኮሚሽነር ስም፡-------------------------------------------

ፊርማ፡-------------------------------------------

ቀን፡-------------------------------------------

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን

ጥር፣ 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ